# ብዕርን በማፈን ማንነትን መግደል አይቻልም!

አሥራደው (ከፈረንሳይ)



ብዕር እስትንፋስ ናት፤ ብዕር ሕይወት ናት፤ ብዕር በሥጋ ወደሙ ላይ ሕይወትን ዕፍ በማለት ሥጋን ነፍስ የምትዘራ ከዕውቀት ዛፍ የምትገኝ ፍሬ ናት፤ ያቺን ፍሬ የቀመሰ ሁሉ ማንነቱን አውቋልና ያለ እሷ መኖር አይቻለውም፤ እሷን ያጣ እለት በጨለማ ይከበባል፤ የጨለማ ሕይወት ላለመኖር ሲል እስከ ሕይወት መሰዋዕትነት ድረስ ዋጋ ይከፍላል፤ ከራሱ አልፎ ድንበር ሳይገድበው፤ ቀለም ሳይደልለው፤ የዘር ሃረግ ሳይጠልፈው፤ ከአድማስ እስከ አድማስ የነፃነት ጩራ ለመላው የሰው ልጅ ፍንጥቅ እንዲል ያደርጋል።

ብዕር ጦር ነው የማንነት ማስከበሪያ፤ ለማንነት መግለጫ ሲባል ከአፎቱ የሚመዘዝ ጎራዴ፤ እንደ አያያዙና አወራወሩ፤ እንደ አቋቋሙና አወነጫጨፉ፤ እንደ ጉልድፍናውና የሠላ እንደበቱ፤ እንደ ጠረኛነቱና ሠላማዊነቱ፤ እንደ ቁጣና ትዕግሥቱ፤ እንደ ይቅርታውና ምህረቱ፤ አንዱን ሲያሳዝን ሌላውን ያስፈነድቃል፤ አንዱን ሲያቆስል ሌላውን ያክማል፤ አንዱን ሲገድል ሌላውን ያድናል፡ በፍትሕ የበላይነት የሚያምን ጀግና ነውና! እናም **ብዕርን በማፈን ማንነትን መግደል አይቻልም!**

እልፍ ሲሉም ብዕር ፍቅር ነው፤ ለሚያፈቅሩት ሁሉ የፍቅር እንባ ስቅስቅ ብሎ ያነባል። ብዕር ሠላም ነው፤ ብዕር መካሪ ነው፤ ብዕር ሽምጋይ ሆኖ ሠላምን በማውረድ ያስታርቃል፤ ያስተቃቅፋል፤ ይቅር ያባብላል፤ ያከባብራል፤ ያነፋፍቃል፤ አንድ አድርጎ የሠላምን ችቦ በአንድነት በማንቦግቦግ፤ የአንድነት፤ የውንድማማችነትና የእኩልነት

መዝሙር፤ ድምፅን ከፍ አድርጎ በማዘመር፤ አንባ እያስተናነቀ ልብን በደስታ ሞልቶ፤ ጮቤ እያስረገጠ ያስፈነድቃል፤ ያዘፍናል፤ ያስቃል፤ ያንከተክታል፤ ነፍስን በሃሴት ሞልቶ ተስፋን በማጫር ከአድማስ ባሻገር ጮራን ይፈነጥቃ።

ያለ ብዕር የሚኖር ሙት ነው፤ ሕይወትን መተንፈስ የማይቻለው በቁሙ የሞተ በድን። የዕውቀት ፍሬን ጣዕም ሳያላምጥ፤ የነፃነት ብርሃን ሳያይ፤ ልቡን የፍቅር ረመጥ ሳያግመው፤ ገላውን የፀሐይ ጮራ ሳይሞቀው፤ ፊቱ በደስታ ሳይፈካ፤ ፈገግታ ከንፈሮቹን ሳያንኳኳ፤ ልቡ ፍቅርን ሳይረጭ፤ በሆዱ ጥላቻን አርግዞ፤ በልቶ በማራት ብቻ በመርካት፤ ሌላ ሕይወት፤ ሌላ አድማስ፤ ሌላ አስተሳሰብ፤ ሌላ ሰው፤ሌላ ፍጡር፤ ሌላ አገር መኖሩን ሳይረዳ፤ በጨለማ ተከቦ የጨለማ ኑሮ እንደኖረና ልቡንና ገላውን እንዳጨለመ ጨልሞበት ወደ መቃብር የሚያልፍ ትርክርክ ፍጡር! አስቲ ማን ነው ይኸንን አሳማ ፍጡር መሆን የሚሻ?!

የሚያስቡት በአይምሯቸው ሳይሆን በሆዳቸው ስለሆነ ሰው ሁሉ የሚኖረው እንደ እነሱ በእህል ብቻ ይመስላቸዋል። ከሥጋዊ ምቾት በባሰ በሕሊና ረሃብ የሚሰቃዩ ዜጎችን ጩኸት ለመረዳት አይምሯቸው በስብ ስለደለበና የጀሯቸው ብራና በጮማ ስለተደፈነ የማዳመጥ ችሎታቸው ውሱን ነው።

የነሱ እርካታ ሆድ በመሙልስት ብቻ በባዶ ኳኳታ ጭንቅላትን ጠቅጥቆ፤ በወያኔያዊ ፕሮፓጋንዳ ሕዝብን በማደንዘዝ፤ የአገር ሃብት መዝረፍና ማዘረፍ፤ ሕዝብ በረሃብ እየረገፈ፤ በንቅዘት (ሙስና) ተዘፍቆ የጉራ ልማት ማውራት፤ ድሃ ገበሬዎችን ከመሬታቸው አፈናቅሎ ለቀማኛ የውጪ ከበርቴ መቸብቸብ፤ አዲሱን ትውልድ እዳ ከፋይ በማድረግ ኢትዮጵያን በብድር ማጥ ውስጥ መክተት፤ ዘረኝነት መመሪያቸው፤ ውሸት ክብራቸው፤ ክህደት ኩራታቸው፤ ሽብር ተግባራቸው፤ ጎሰኝነት ባንዲራቸው፤ ሃቅ ተናጋሪዎችን ጠላታቸው፤ ባደረጉባት የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሃቅን መጻፍ አሸባሪ ተብሎ ያስከስሳል። ጠብ መንጃ በጁ የያዘ አሸባሪው ባሸበረ፤ ብዕር የጨበጡ ሠላማዊ ጋዜጠኞች፤ አሸባሪ ተብለው ታሰሩ። ፍየሏ ነብሩን በላችው! የሚሉት ጠንባራ ውሸት ይሏ ችኋል ይህ ነው።

« እንዲህ ያለ ዘመን የተገላቢጦሽ፤
አህያ ወደ ቤት ውሻ ወደ ግጦሽ »

ብሎ በኃይሉ እሼቱ የዘፈነው ለካ የዛሬውን ዘመን አንድዬ አስመልክቶት ኖሯል?! አፈሩ ይቅለልህ የኔ ወንድም! ምነው ላገራቸው ፍቅርና ክብር ያላቸው ዜጎች አልበረክት አሉን? ሁሉም ጥለውን « ይችን አገር አደራ!» ብለው አደራ ጥለውብን አለፉ?! ታዲያ ለአደራ የምንበቃውስ ስንቶቻችን እንሆን?!

(በኃይሉ እሸቴን ለማያውቁ: የጥንቱ ፖሊስ ሠራዊት የሙዚቃ ባልደረባ፤ እንደ እንጀራ ባቋራጭ፤ ጉቦና: ሌሎች የሕዝባችንን ጩኸቶች እያቀነቀነ በባለስልጣናት ጡጫ

*አተኮረኮመ: ሳይንበረከክ ህይወቱን ያሳለፈ ብርቅዬ አቀንቃኝ ነው፤ ከሂሩት በቀለ፤ ከዓለማየሁ እሼቴና ከሌሎች ጋር ሆኖ ::*

*በነገራችን ላይ እስቲ የዓለማየሁ እሸቴን፤ እናት የእንጀራናት፤ ሰቀሽ አታስቂኝ፤ ምንትችቴ ምድሪቱ፤ የሰው ቤት የሰው ነው፤ ቆጨኝ መሳሳቴ፤ የሚሉ ዘፈኖቹን ፈልጋችሁ አድምጡ፤ ዛሬ ላይ ቆሞ ትላንትን በትውስታ ለመቃኘት፤ ነገን ከሩቁ ተመልክቶ ለማለም ማለፊታ የአርቆ መመልከቻ መነጥር ናቸው ::) ወደ ጅምሬ ልመለስ!*

*እኛ በኢትዮጵያዊነት ዐይን ስንመለከታቸው፤ እነሱ በዘረኝነት መነጥር ለሚያጉረጠርጡብን « ዘረኞች » የምንላቸው፤ ብዕር ሲታፈን ሰውነት ይታመማል፤ ሰብዕና ይቀጭጫል፤ ነፍስ ይጨነቃል፤ ሠላም ይጠፋል፤ ነፃነት ይገሠሣል፤ በደል ይነግሣል፤ አምባገነንነት ተንሰራፍቶ አገር ይሞታል ::*

*በዚህም የሕዝብ አደራ ተንዶ አገር ይታመሳል፤ እምነት ይሸረሸራል፤ ሕዝባችንን ጭዳ ለማድረግ ረሃብና ጦርነት ፈረሳቸውን ጭነው ሊጋልቡት ያሶመሱማሉ፤ ያ እንዳይሆን አማራጩ ሁለት ነው ::*

*አንድም፤ ብዕርን እንድትተነፍስ በመፍቀድ ወደ ሠላምና ፍቅር፤ ይቅርታ፤ መቻቻል፤ መተጋገዝና ከ ኢህአዴግነት ይልቅ ወደ ሁሉን አቀፍ አብሮ አደግነት መርህ መሸጋገር ::*

*አለያም : የብዕርን ቁርቤ አንቆ ሠላም በማጣት ኮሽ ባለ ቁጥር እየበረገጉ ሁሉን ጠላት አድርጎ፤ በመከልከል ላይ: መከልከልን እየደራረቡ፤ በመከልከል አጥር ታጥሮ: ሁሉን ከልክሎ፤ ሁሉን ለእኔ ብቻ በሚል: የሰስታም ልክፍት ተለክፎ: በድንቁርና በብቸኝነት መሞት ::*

*እድሉ፤ ጊዜውና የሕዝብ ፈቃድ እያለ: ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር መታረቅ ያቃተው መሪ፤ የበደል ቋቱ ሞልቶ ከገነፈለ በኋላ፤ ሕዝብ ቢለመን ይቅር የሚልበት ልቡ በበደል ክምር ከተናደ በኋላ ይቅር የሚልበት ልብ ስለማይኖረው፤ ያ ከመሆኑ በፊት ልቦና ላለው ማምሻም ሕይወት ናትና ዛሬም አልመሸም !!*

*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!*
*እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ !!*

*ሰኔ 30 / 2003 ዓ.ም. (July 7/2011)*

*በነጻ ጋዜጠኝነት ተሰማርተው በወያኔ ወከባ፤ እስር ስደትና መጉላላት ብሎም ሞት ለደረሰባቸው የነጻው የጽሑፍ፤ የምስል፤ የተንቀሳቃሽ ምስሎች መረጃ (free Presse) አባል ለሆኑ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን መታሰቢይ ትሁንልኝ::*